# ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የሚጸለይ የውሳኔ ጸሎት

*ፈጣሪ በሆነው ሁሉን ቻይ አንድ አምላክ አምናለሁ።*

*ሌሎች አማልክትን ሁሉ እክዳለሁ።*

*እግዚአብሔርንና ሰዎችን መበደሌን እናዘዛለሁ። ይህንንም በማድረጌ በእግዚአብሔርና በሕግጋቱ ላይ አመፅን ፈፅሜያለሁ።*

*ራሴን ከኃጢአት ማዳን አይቻለኝም።*

*ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑንና ሞትን ድል አድርጎ የተነሳ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ። በመስቀል ላይ በኔ ፋንታ ሞቶ የኃጢአት ቅጣቴን ከፍሎልኛል። ስለ እኔም ከሙታን ተነስቷል።*

*ከኃጢአቴ እመለሳለሁ።*

*በመስቀል ላይ የተገኘውን የክርስቶስን ይቅርታ እለምናለሁ።*

*ይህንንም የይቅርታ ስጦታ አሁን ተቀብያለሁ።*

*እግዚአብሔር አባቴ መሆኑን ተቀብዬ የእርሱ መሆንን እሻለሁ።*

*የዘላለምን ሕይወት እፈልጋለሁ።*

*ሕይወቴን በሙላ ለክርስቶስ ሰጥቼ ከዛሬ ጀምሮ እርሱ ይመራኝ ዘንድ እገዛለታለሁ።*

*ሌሎች መንፈሳዊ ቃል ኪዳኖችን በሙሉ ክጃለሁ። ሸሃዳንና በኔ ላይ ያለውን ቁጥጥር በሙሉ እክዳለሁ።*

*ሰይጣንንና ክፋትን ሁሉ እክዳለሁ። ከክፉ መንፈሳውያን ሥልጣናት ጋር ያደረኳቸውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆኑ ስምምነቶችን በሙሉ እክዳለሁ።*

*ከእግዚአብሔር ያልሆነ ሥልጣን በኔ ላይ ይኖራቸው ዘንድ ከሌሎች ጋር የገባኋቸውን ስምምነቶች ሁሉ አፍርሻለሁ።*

*በማንኛውም ሁኔታ በኔ ላይ ተፅዕኖ እያደረገ የሚገኝ ዘር ማንዘሮቼ የገቡትን ቃል ኪዳን በሙሉ አፍርሻለሁ።*

*በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ያልመጣ ማንኛውንም ስነ ልቦናዊ ወይም መንፈሳዊ ኃይል ሁሉ እክዳለሁ።*

*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይሰጠኝ ዘንድ እለምናለሁ።*

*አባቴ እግዚአብሔር ሆይ ላንተና ላንተ ብቻ ክብርን ማምጣት እችል ዘንድ አቤቱ አርነትን ስጠኝ።*

*አንተን እንዳከብርና ሌሎችን እንድወድ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በውስጤ አኑር።*

*ራሴን ለእግዚአብሔር አምላኬ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መቀደሴን በሰዎችና በመንፈሳውያን ኃይላት ሁሉ ፊት አውጃለሁ።*

*የሰማይ ዜጋ መሆኔን አውጃለሁ። እግዚብሔር ጠባቂዬ ነው። በዘመኔ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንደ ጌታዬ ለመከተል በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ምርጫዬ አድርጌያለሁ።*

*አሜን።*